# ሚዲያ እንደ ሀገሩ ወፍ መጮህ ሊጮህ ይገባል!

**ዘሪሁን ከበደ** 07/29/14

ዛሬ ዓለማችንን ወደ አንድ መንደርነት በመቀየር ላይ ከሚገኙ ምክንያቶች አንዱ መገናኛ ብዙሃን መሆናቸው የሚታበይ አይደለም፡፡ ታዲያ ስለመገናኛ ብዙሃን ስናነሳ ዛሬ የትናንት ውጤት በመሆኑ የመስኩን ባለውለታዎች ማውሳቱ የግድ ይላል፡፡ በመሆኑም ለሚዲያ መፈጠርና ማደግ ባለውለታ ከሆኑት መካከል ለአንጋፋው የህትመት ሚዲያ መወለድና መመንደግ ባለውለታ የሆነውን ጉተንበርግ፣ ለብሮድካስት ሚዲያው ደግሞ የሬዲዮው ማርኮኒ እንዲሁም የቴሌቪዥን ፈጣሪው ቤርድ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

እርግጥ ከዓለማችን የዕድገት ሁኔታ ጋር አብረው እያደጉ ዛሬ ላይ የደረሱት መገናኛ ብዙሃን አዎንታዊ ሚናቸው ከፍተኛ እንደሆነ ሁሉ አሉታዊ ጎናቸውም በቀላሉ የማይታይ መሆኑን ታሪክን አጣቅሰን መመልከት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ለሀገራዊ ልማት መፋጠንና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታው መጎልበት ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ የመገናኛ ብዙሃን የመኖራቸውን ያህል፤ ሀገራትን ለከፍተኛ ቀውስና ዕልቂነት የዳረጉ ሚዲያዎች በዓለማችን በመስተዋላቸው ነው፡፡

ታዲያ የህዝቡን የልማትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተጠቃሚነት የማፋጠን ሚና የተጫወቱ የኤሺያና የላቲን አሜሪካ ሀገሮች መገናኛ ብዙሃንን መጥቀስ እንደሚቻለው ሁሉ፤ በአንጻራዊነት ለሩዋንዳውያን የእርስ በርስ ጦርነትና ከፍተኛ እልቂት መንስዔ የሆነውን የሀገሪቱን ሬዲዮ መመልከቱ እውነታውን ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡ እርግጥም የመገናኛ ብዙሃን በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ መዋል ካልቻሉ የሚያስከትሉት አደጋ በቀላሉ የሚገመት እንደማይሆን መረዳት ይቻላል፡፡

እንደሚታወቀው የመገናኛ ብዙሃንና የሀገራቸው ፖለቲካል- ኢኮኖሚ ትስስር ያላቸው ናቸው። ባለቤትነታቸውና ሚናቸውም የሚወሰነው በሥርዓቱ መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡

በሌላ አገላለጽ የአንድ ሀገር መገናኛ ብዙሃን የሥርዓቱ ነጸብራቅ ናቸው ማለት ነው— “ወፍ እንዳገሩ ይጮሃል” እንዲሉ አበው።

ከዚህ አኳያ የሀገራችንን የቅርብ ጊዜ ትውስታን ስንመለከት፤ ሁለት የተለያዩ የፖለቲካል- ኢኮኖሚ ሥርዓቶችንና የመገናኛ ብዙሃን ሚናን እናገኛለን፡፡ የደርግ መንግስት ይከተለው የነበረው ፖለቲካል- ኢኮኖሚና መገናኛ ብዙሃን ባለቤትነታቸውና ሚናቸው የሥርዓቱ ነጸብራቅ ነበሩ፡፡

ሁላችንም እንደምንገነዘበው ወታደራዊው መንግስት ከሚከተለው ፖለቲካል-ኢኮኖሚ ሥርዓት አኳያ ሃሳብንና አመለካከትን በነጻነት የመግለጽ መብት ተገድቦ ዘመናትን ተሻግሯል፡፡ የመገናኛ ብዙሃኑ ባለቤትነትም በመንግስት ብቻ ከመያዙ ባሻገር፤ የቅድመ ምርመራ ህግም ዋነኛው የማፈኛ ዘዴ ሆኖ አገልግሏል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የመገናኛ ብዙሃን ሚና በዋነኛው የሀገራዊው ድህነትንና ኋላቀርነት የመቅረፍና ለህዝብ የዴሞክራሲ መብቶች መከበር የዘመናት ጥያቄ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ፤ በሥርዓቱ ህልውና ቀጣይነት ላይ ሚያተኩር የፕሮፓጋንዳ ሥራ ተጠምዶ ዘመናትን ተሻግሯል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የደርግ መንግስትን መገርሰስ ተከትሎ የተፈጠረው የፖለቲካል- ኢኮኖሚ ሥርዓት ነፀብራቅ የሆነ መገናኛ ብዙሃን አሰራር መዘርጋት ተችሏል፡፡ በዚህም ለዘመናት የተሻገረው የፕሬስ ነጻነት ጥያቄ ምላሽ አግኝቷል፡፡ የቅድመ ምርመራ አሰራርም አክትሟል፡፡

ሀገሪቱ የተቀናጀ የመገናኛ ብዙሃን የባለቤትነት አቅጣጫን በመከተሏ በመንግስት ብቻ ታጥረው ከቆዩ ሚዲያዎች ይልቅ በብዙ እጥፍ የሚበልጡ የግሉ የህትመት ሚዲያ ውጤቶችን መመልከት ተችሏል፡፡ በዚህም ዜጎች አመለካከታቸውንና ሃሳባቸውን በነጻነት የመግለጽ መብታቸው ተከብሮ በሂደት እየጎለበተ ነው ፡፡ በመሆኑም መገናኛ ብዙሃን ከፖለቲካል- ኢኮኖሚው ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዳላቸው መገንዘብ አዳጋች አይሆንም፡፡

ከዚህ በመነሳትም በአሁኑ ጊዜ የመገናኛ ብዙሃንን የአሰራር ፍልስፍና የሚያመላክቱ ሁለት አስተሳሰቦች ይስተዋላሉ የእነዚህ አስተሳሰብ ምንጭ ደግሞ ፖለቲካል- ኢኮኖሚው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

የመጀመሪያው አስተሳሰብ የመገናኛ ብዙሃንና የጋዜጠኞነት ሙያ ዋነኛ ተግባር ዜጎች በነጻነት ራሳቸውን በራሳቸው እንዲመሩ የሚያስችል መረጃ ማቅረብ ነው የሚል የሊበራል ፖለቲካ ኢኮኖሚ አቀንቃኞች አቋም ነው፡፡ ይህም መገናኛ ብዙሃንን ከፖለቲካል- ኢኮኖሚው የተለየ ህልውና እንዳላቸው የማስመሰል ጥረት ነው፡፡ ይህ አመክንዮ የመገናኛ ብዙሃኑ ተግባር የዜጎችን መብት በማስከበር ብቻ የተወሰነ ሊሆን ይገባል የሚል አስተሳሰብ ውጤት መሆኑ ግልፅ ስለሆነ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የዚህ አስተሳሰብ አራማጆች ዜጎች በመገናኛ ብዙሃኑ በየዕለቱ የሚያገኙት መረጃ እነርሱ የሚፈልጉትና በተግባርም ለነጻነታቸውና ራሳቸውን በራሳቸው ለመምራት የሚያስችል መረጃ ማቅረብ አስቸጋሪ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ይህ አስተሳሰብ በጥቅሉ ሲታይ መገናኛ ብዙሃን ተግባርና ሚና በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የፖለቲካል- ኢኮኖሚው ነጸብራቅ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚህም ባሻገር መገናኛ ብዙሃኑ የፖለቲካ ኢኮኖሚው የበላይ አካል የሚቆጣጠራቸው በመሆናቸው በኢኮኖሚ የበላይነትና በፖለቲካ አስተሳሰብ ልዕልና መካከል ያለው ቀጥተኛ ትስስር የመገናኛ ብዙሃንና የፖለቲካል- ኢኮኖሚው ግንኙነትም ጠንካራ ትስስር ያለው ይሆናል፡፡

የኒዮ- ሊበራል ሥርዓት የዘረጉ ሀገራት መገናኛ ብዙሃን ንብረትነታቸው የግሉ ባለሀብት በመሆኑ፤ ተቋማቱ በመረጃ ሽያጭ የሚተዳደሩና እንደ ንግድ ተቋማት የሚታዩ ናቸው፡፡ ተግባራቸውና የአሰራር ፍልስፍናቸው የመንግስትን የሥራ ሂደት መቆጣጠር ብቻ ነው፡፡

ሁለተኛው አስተሳሰብ ደግሞ የመገናኛ ብዙሃንን የተቀናጀ ባለቤትነት ሞዴል በመከተል በህዝብ፣ በግልና በማህበረሰብ ባለቤትነት የሚተዳደሩ ሚዲያዎች የመኖር አስፈላጊነትን አቋም የሚገልጹ ወገኖች ምልከታ ነው፡፡

የመገናኛ ብዙሃን ሚና የዜናች የመረጃ ልውውጥና የክርክር መድረክነት የሚያገለግል፣ በህዝብና በመንግስታት እንዲሁም በንግድ ተቋማት መካከል ጤናማ ግንኙነት መፍጠር፣ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ የሃሳብ ክርክር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማጎልበት መሆን ይኖርበታል፡፡

የህዝቡ ባህል፣ ልምድና እሴት መገለጫና ማሳደጊያ መድረክ የሆነ፣ የመንግስት ሥራን በግልጽነትና በተጠያቂነት የሚያሳድግ፣ የመልካም አስተዳደርና የሙስና ችግሮችን የሚያጋልጥ እንዲሁም የኢኮኖሚ ልማትን ማፋጠንና ውጤታማነቱን ማረጋገጥ የመገናኛ ብዙሃን ሚና መሆን እንዳለበትም ያስረዳል፡፡

ታዲያ ይህ እሳቤ የመገናኛ ብዙሃን የልማት አቅጣጫዎች መገናኛ ብዙሃን በባለቤትነትም ሆነ በሚያቀርቡት የመረጃ ይዘት ብዝሃነትን ማስተናገድ እንደሚኖርባቸው የሚያመላክት አቅጣጫ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ እናም ከዚህ ሃቅ የምንረዳው ነገር ቢኖር 'በልክ የተሰፋ ጥብቆን' የማጥለቅ አስፈላጊነትን ይሆናል፡፡

እርግጥም ከመጠን በላይም ሆነ በታች የሆነን ነገር ማጥለቁ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝን የሀገሬ ሰው "ሰው እንደ ቤቱ እንጂ እንደ ጎረቤቱ አይኖርም" እንዳለው፣ የመገናኛ ብዙሃን ሚናም ከሀገራዊው ፖለቲካል-ኢኮኖሚ ስርዓት ጋር የሚጣጣም መሆን ይገባዋል፡፡

ምክንያቱም ከሀገራዊው ፖለቲካል-ኢኮኖሚ ፍላጎት ጋር የማይጣጣም መገናኛ ብዙሃን ልክ 'ካለ ቦታው የበቀለ ምንትስ' እንደሚባለው በመሆኑ ጠቀሜታውና ተፈላጊነቱ እዚህ ግባ ሊባል የማይችል ስለሆነ ነው፡፡

እናም ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት የመገናኛ ብዙሃንና የፖለቲካል -ኢኮኖሚ ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ "ወፍ እንዳገሩ ይጮሃል" የሚለው አባባል የመገናኛ ብዙሃን የአሰራር ፍልስፍና መሆን የግድ ይለዋል፡፡

እንደሚታወቀው የሀገራችን መንግስት የልማታዊ ዴሞክራሲ ሥርዓትን በመከተል ላይ የሚገኝና ለተከታታይ አስር ዓመታት ባለ ሁለት አሃዝ ዕድገት በማስመዝገብ ውጤታማነቱን ማስመስከር የቻለ ነው፡፡

ይህም ሀገሪቱ ከነበረችበት የድህነትና የኋላቀርነት አረንቋ ለማውጣት የተከተለው የልማታዊ አስተሳሰብና ፍልስፍና የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ አማራጭን ለመከተል ያካሄደው ጥረት ውጤት መሆኑ አይታበይም፡፡

ታዲያ እዚህ ላይ አንድ ትልቅ ቁም ነገርን ማስተዋል ይገባል። ይኸውም ከኒዮ - ሊበራል ፖለቲካል- ኢኮኖሚ አስተሳሰብና ፍልስፍና ውጭም ማደግ የሚቻል መሆኑ ነው፡፡ ሀገራዊ ዕድገትን ማስመዝገብ የሚቻለውም በተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ በሚነደፍ ፖለቲካል -ኢኮኖሚ ሥርዓት እንጂ የሌሎችን አካሄድ እንዳለ ለመገልበጥ በመሞከር አለመሆኑንም እንዲሁ፡፡

በእርግጥ የኢፌዴሪ መንግስት ሀገራዊ ተጨባጭ ሁኔታን ያገናዘበ ፖለቲካል -ኢኮኖሚ ሥርዓት መዘርጋቱ ያልተዋጠላቸው አክራሪ ኒዮ-ሊበራሎች ፍላጎታቸውን በኃይል ለመጫን ሙከራ ማድረጋቸው አይዘነጋም፡፡ በሁኔታው የተሳለቁና በየመድረኩም ትችታቸውን ያዥጎደጎዱ ኃይሎችም አልታጡም፡፡

ያም ሆኖ ግን "ማየት ማመን ነው" እንደሚባለው ሀገራዊ የምጣኔ ሀብቱን ማሳደግ የቻለው የኢፌዴሪ መንግስትን ዱካ መከተል ተመራጭነቱ እያደገ ለመምጣት የመቻሉ እውነታ የመገናኛ ብዙሃኑ ምርጫም ልማታዊ መሆን እንዳለበት ያሳየናል፡፡

እንደሚታወቀው የየትኛውም ሀገር ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ልማትን ማፋጠንና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን የመገንባት አቅጣጫን የሚከተል ነው፡፡ ለዚህም ስኬታማነት የመገናኛ ብዙሃን ሚና ከፍተኛ እንደሆነ አያጠያይቅም፡፡

በመሆኑም የልማታዊውና ዴሞክራሲያዊ መንግስታት የፕሬስ ነጻነትን የሚያሰፍኑ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ከዚህ አኳያ የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ስንመለከት፤ የተቀናጀ የመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት የሚከተል፣ የመገናኛ ብዙሃኑ ሚና ደግሞ ለልማቱ

መፋጠንና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባህል ግንባታ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ የሚያስችል ዕድልን መፍጠር የቻለ ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ በህገ - መንግሥቱ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ የፕሬስ ነጻነትን አስመልክቶ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፣ ሃሳቦችና አመለካከቶች በነጻ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል፤ ፕሬስ በተቋምነቱ የአሰራር ነጻነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የህግ ጥበቃ ይደረግለታል የሚል ግልፅ ድንጋጌ ተቀምጧል፡፡

ይህም ሀገሪቱ ከምትከተለው የፈጣን ልማትን የማረጋገጥ ጥረትና ለዴሞክረሲያዊ ሥርዓት ግንባታው መፋጠን የመገናኛ ብዙሃን የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ የሚያስችል ነው፡፡

ሁላችንም እንደምናውቀው ልማትን የማረጋገጡ ጉዳይ ሀገራዊ ህልውናን የማስጠበቅ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የዘመናት የህዝብ ጥያቄ የሆነው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታን ማፋጠንም ከልማቱ ጋር አብሮ የሚታይ ህልውናን የማረጋገጥ ጉዳይ ነው፡፡

በመሆኑም የሀገራችን የመገናኛ ብዙሃን ሚናና የአሰራር ፍልስፍና ከነባራዊው ሀገራዊ የለውጥ ፍላጎታችንና በብዝሃነት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ አንድነት የመገንባት ዓላማ ያለው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ይህን ለማሳካት ድርሻቸው ከፍተኛ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ዛሬ በከፍተኛ ዕድገት ላይ የሚገኙ የኤሺያና የላቲን አሜሪካ ሀገሮች ለውጥ በማስመዝገብ ረገድ የቀረፁት የመገናኛ ብዙሃን የባለቤትነት ሚና አስተዋጽኦ የላቀ እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

የእነዚህ ሀገራት መገናኛ ብዙሃን በመንግስት፣ በህዝብና በግል ባለቤትነት ስር ሆነው ሚናቸውም ይመሳሰላል፡፡ የመገናኛ ብዙሃኑ ልማትንና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታን የማሳካት አጀንዳ ላይ ትኩረት ሰጥተው በመስራት የበኩላቸውን ሚና ይጫወታሉ፡፡

በእርግጥ ከእነዚህ ሀገራት በተቃራኒ የሊበራል የመገናኛ ብዙሃን የአሰራር ስርዓትን እንደ አማራጭ የሚከተሉ ታዳጊ ሀገሮች መኖራቸው አልቀረም፡፡ ይሁንና እነዚህ መገናኛ ብዙሃን ለሀገራዊው ልማት ከሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ይልቅ ለውድቀት ሲዳረጉ ይስተዋላሉ፡፡

ምክንያቱም የሊበራል የመገናኛ ብዙሃን እንደ አራተኛው የመንግስት አካል ተደርገው ስለሚታዩ ከተጨባጭ ሁኔታቸው ጋር አብሮ ስለማይሄድ ነው፡፡ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ግን ይህ አይነቱ አሰራር ቦታ የለውም፡፡ ሚዲያ የስርዓቱ ነፀብራቅ እንጂ አራተኛው የመንግስት አካል ተደርጎ አይወሰድም።

ለምን ቢሉ ሀገራችን ከምትከተለው ፖለቲካል -ኢኮኖሚ ሥርዓት ጋር ተያይዞ የመገናኛ ብዙሃን የተቀናጀ ባለቤትነት ሞዴል በመከተል፤ በህዝብ፣ በግልና በማህበረሰብ ባለቤትነት የሚተዳደሩ መገናኛ ብዙሃን የሶስቱ የመንግስት አካላት ደጋፊዎች እንጂ ውሳኔ ሰጪ ስላልሆኑ ነው፡፡

እናም የሀገራችን የመገናኛ ብዙሃን ዋነኛ ተልዕኮ ሊሆን የሚገባው ልማትን የማፋጠን፣ የመንግስትንና የህዝቡን እንዲሁም የባለሃብቶችን የፀረ-ድህነት ትግል የማገዝና የልማት አጀንዳን ቀዳሚ በማድረግ ኃላፊነታቸውን መወጣት ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ለዘመናት የዘለቀው የህዝቦች የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጥያቄ ምላሽ ለሚሰጠው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ስኬታማነት የህዝብን ተሳትፎ የሚያጎለብት አጀንዳ በመንደፍ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ማበርከት ይኖርባቸዋል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም። የመገናኛ ብዙሃኑ የመንግስት አሰራር ግልፅነትንና ተጠያቂነትን በማረጋገጥ፣ ሙስናንና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በማጋለጥ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱን መደገፍ ትኩረት የሚሰጡት አጀንዳ ሊሆን ይገባል፡፡

ሁለንተናዊ የኑሮ መሻሻልን፣ የባህል ዕድገትና ብዝሃነትን በማክበር ሚናቸውን እንዳለባቸውም እንዲሁ፡፡ ታዲያ መገናኛ ብዙሃኑ በዚህ መንገድ መጓዝ ካልቻሉ

ለሀገራዊው ፈጣን ልማትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚያግዙ ከመሆን፣ በተቃራኒው አፍራሽና የሊበራል ኃይሎች ፍላጎትን የማሳካት ሚና የሚጫወቱ መሆናቸው አይቀሬ ነው፡፡

በመሆኑም በፖለቲካል - ኢኮኖሚው የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በብቃት በመጠቀም ፈጣን ለውጥ ለማምጣት መንቀሳቀስ እንዳለባችው መዘንጋት አይኖርባቸውም፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ የሀገራችንን የመገናኛ ብዙሃን ተጨባጭ ሁኔታን በደምሳሳው መዳሰሱ አስፈላጊ ይመስለኛል፡፡

እርግጥ የደርግ መንግስት መውደቅን ተከትሎ በተፈጠረው የፕሬስ ነጻነት ሳቢያ በርካታ ሚዲያዎች መፈጠራቸው የትናንት ትውስታችን ነው፡፡ እነዚህ የመገናኛ ብዙሃን ለአዲሱ ሥርዓት ግንባታ ስኬት አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ ሚና መጫወታቸው አይዘነጋም፡፡

በተለይም የኤሌክሮኒክስ ሚዲያው ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን ለማጠናከር የሚያስችሉ የልማት፣ የሠላምና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ላይ ህዝቡን በስፋት ለማሳተፍ ቀጣይነት ያለው ጥረት አድርገዋል፡፡ መገናኛ ብዙሃኑ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦችን የእምነትና የፆታ እኩልነት ለማረጋገጥ የሚያግዙ ችግሮች ሲያጋጥሙ የመፍትሄ አቅጣጫዎች የሚያመላክቱ ስራዎችን ከማከናወናቸው ባሻገር፤ በሀገራችን ላይ የተቃጣው የፀረ - ሉዓላዊነት አደጋን ለመቀልበስ ህዝቡ በአንድ መንፈስ ወራሪ ኃይሎችን በጽናት እንዲታገልና ሉዓላዊነቱን እንዲያስከብር የሚያስችሉ ተግባራትን አከናውነዋል፡፡

ልክ እንደ ኤሌትሮኒክስ ሚዲያው ሁሉ የህትመት ሚዲያውም የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ በተለይም የመንግስት የህትመት ሚዲያ ከኤሌትሮኒክስ ሚዲያው ያልተናነሰ ስራ ሰርቷል። በአንፃሩ ግን የግሉ የህትመት ሚዲያ ተግባሩን በሁለት መልኩ ማከናወኑን ማየት እንችላለን፡፡

ይኸውም በአንድ በኩል ለልማቱ መፋጠንና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱ ግንባታ የሚያግዝ ተግባራትን ያከናወኑና የፖለቲካል - ኢኮኖሚውን ሥርዓት መሰረት በማድረግ የተንቀሳቀሱ ናቸው– ቁጥራቸው እጅግ አነስተኛ ቢሆንም።

እነዚህ የህትመት መገናኛ ብዙሃን የህዝቡን የመረጃ ፍላጎትና የንባብ ባህል ለማጎልበት የበኩላቸውን ሚና የተጫወቱ ሲሆን፤ በምርጫ ወቅትም የህዝብን የመረጃ ፍላጎት ለማሟላት ሰፊ ጥረት አድርገዋል፡፡ በመሆኑም የፖለቲካል- ኢኮኖሚውን ሥርዓት መነሻ በማድረግ፤ ለፈጣን ልማቱ ቀጣይነትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታው መጎልበት የልማታዊነት አቅጣጫን ተከትለው የበኩላቸውን ሚና ተጫውተዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ህገ - መንግስታዊ ሥርዓቱን ከመገንባትና ለልማቱ መፋጠንና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታው መጎልበት ኃላፊነታቸውን ከመወጣት ይልቅ በመቃወም ላይ ያተኮሩ የግል ህትመት ሚዲያ ውጤቶች በሰፊው ተስተውለዋል፡፡

እነዚህ የግል ህተመት ሚዲያዎች የፖለቲካል-ኢኮኖሚው ሥርዓት በፈጠረው የፕሬስ ነጻነት ድባብ ውስጥ ተወሽቀው ህገ- መንግስታዊ ሥርዓቱን ለማፍረስ ከፍተኛ ጥረት ማካሄዳቸው የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው–ዛሬም ድረስ የዘለቀ ጭምር።

መገናኛ ብዙሃኑ የህዝብ የመረጃ ምንጭ፣ የውይይትና የክርክር መድረክ ሆነው ከማገልገል ይልቅ፤ ህገ - መንግስቱን ለማይቀበሉና ሥርዓቱን የሚቃወሙ ኃይሎች ልሳን ሆነው የአፍራሽነት ተግባራቸውን ለመወጣት ሞክረዋል፡፡ ከመሰንበቻው በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትና በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት አማካኝነት በገለልተኛ አጥኚዎች በሰባት መፅሔቶች ላይ የተካሄደው ጥናትም የዚህ አባባሌ አስረጅ ነው።

እርግጥ ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት የራሱ ልሳን የሆነ የህትመት ሚዲያን ማቋቋም ይችላል፡፡ በዚህም ፖለቲካዊ አመለካከቱን ወደ ህዝቡ ለማድረስ የሚረዳ ዕድል ተፈጥሮለታል፡፡ ይሁን እንጂ በተለይም አብዛኛው የተቃዋሚ ኃይሎች የፓርቲያቸው ልሳን የሆነ የህትመት ሚዲያ ከማቋቋም ይልቅ፤ በግል ሚዲያ ስም መንቀሳቀሳቸው የተለመደ ተግባር ሆኖ ቆይቷል፡፡

በአሁኑ ወቅትም በግል የህትመት ሚዲያ ስም ከሚንቀሳቀሱት መፅሔቶችና ጋዜጦች መካከል አብዛኞዎቹ የተቃዋሚ ፓርቲ ልሳን ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ ለንባብ የሚያበቁት መረጃ የአንድ ወገን ብቻ መሆኑን መጥቀሱ እውነታውን የሚያረጋግጥ ይሆናል፡፡

ምንም እንኳን የመገናኛ ብዙሃንን በተመለከተ ቀደም ሲል የጠቀስኳቸው ሁለት ዓይነት አስተሳሰቦች ቢኖሩም፣ የጋዜጠኝነት መርሆቻቸው ግን ተመሳሳይነት ያለው መሆኑ አይካድም፡፡ ፍትሃዊነት፣ ርትአዊነት፣ ትክክለኛነት፣ ተጨባጭነት…ወዘተ. ከመርሆቻቸው ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ይሁንና በአሁኑ ወቅት በሀገራችን የሚገኙ አብዛኞዎቹ የህትመት ሚዲያዎች በጋዜጠኝነት መርሆች ላይ ከመመስረትና ተጨባጭ መረጃዎችን ለህዝቡ ከማድረስ ይልቅ፣ ለገበያ ፍጆታ በሚውሉና በ“በሬ ወለደ” የፈጠራ ወሬዎች ታጭቀው የሚታዩ ናቸው፡፡ ከዚህም አብዛኞዎቹ የግል ህትመት ሚዲያ ከመረጃ ዕውነታነት ይልቅ “ስሜታዊነት” የሚባል የአዘጋገብ ዘዴን የሚከተሉ መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግትም።

አዎ! እርግጥም ዛሬ ላይ እነዚህ ሚዲያዎች የመገናኛ ብዙሃን ኃላፊነት የሆነውን ተጨባጭ መረጃን የማሰራጨት ተግባራቸውን እየተወጡ ናቸው ማለት አይቻልም። ይልቁንም ሚዛናዊነት የጎደለውና ለሁለት ወገን እኩል ዕድል ያልሰጠ ሃሳብን ይዞ መቅረብ የእነዚህ ሚዲያዎች ባህሪና መገለጫ እስከመሆን ደርሷል፡፡

እነዚህ የመገናኛ ብዙሃን ወርቃማውና የሙያው ሥነ - ምግባር የሆነው ሀገራዊ ጥቅምን የማስቀደም ተግባር በእነርሱ ዘንድ ስፍራ የለውም፡፡ በዚህም የህዝብን ጥቅም የሚጻረሩ፣ ሀገርና ህዝብን አደጋ ላይ የሚጥሉ መረጃዎችን በስፋት የሚያሰራጩበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡

ህዝብን ከህዝብ ጋር የሚያጋጩ፣ መተላለቅን የሚያስከትሉ፣ የተጀመረውን ሀገራዊ ልማት የማደናቀፍ ሚና ባላቸው መረጃዎች የሚታጨቁት እነዚህ የህትመት ሚዲያዎች፣ እንዲያውም የሚከተሉት የአሰራር ፍልስፍና ምን እንደሆነ በግልፅ የሚታወቅ ነገር የለም።

ምናልባት “ውሻ በበላበት ይጮሃል” የሚባል የሚዲያ የአሰራር ፍልስፍናን ፈጥረው እየተከተሉ ይሆን እንዴ?...እርግጥ ይህን የሚያወቁት እነርሱ ብቻ ናቸው። ለነገሩ አብዛኛዎቹ የህትመት ሚዲያዎቹ የሊበራልም ሆነ የልማታዊ ጋዜጠኝነት ባህሪያትን ካለመከተላቸው የተነሳ ያሉበትን ወይም የቆሙበትን ፍልስፍና ማወቅ እጅጉን አዳጋች ነው፡፡

አቋማቸው በልማታዊነት ሊገለጽ የማይችል ከመሆኑም ባሻገር፤ የሚዲያዎቹ ዓላማና ግብ ሀገራዊ ልማትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱን የሚያረጋግጥ ያለመሆኑና አንድ ፓርቲን ደግፎ በመምጣት የፖለቲካ ጋዜጦች የመሆን አዝማሚያ የሚታይባቸው ሆነው እናገኛቸዋለን።

ይህም የተቀዋሚ ፖርቲዎች በግሉ ሚዲያ የመሸፈን ፍላጎት፣ የሙያተኞቹ አቅም ክፍተት እንዲሁም ሙያውን ጠንቅቆ ባለማወቅና በገቢ ጥገኝነት ምክንያት የሚፈጠሩ ችግሮች መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህም ሳቢያ እንደ ሀገራቸው ወፍ በራሳቸው ዘይቤ መጮህ ተስኗቸው በጥፋት መስመር እየተጓዙ ነው።

ዳሩ ግን የሀገራችን ፖለቲካል - ኢኮኖሚ ሥርዓት ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሀገራችን ልማታዊ መንግስትና ልማታዊ ህዝብ ያላት ናት፡፡ እናም ልማትን ማፋጠን የህልውና ጉዳይ እንደሆነ ተገንዝቦ ለተግባራዊነቱ የሚረባረብ፣ የዴሞክራዊያዊ ሥርዓት ግንባታውም ስር እንዲሰድና ለስኬቱ ሌት ተቀን ባተሌ የሆነ ህዝብና መንግስት ባለባት ኢትዮጵያ ውስጥ፤ የመገናኛ ብዙሃን አጀንዳ መሆን ያለበት ይህን መደገፍና እንዲሳካ ማገዝ መሆን ይኖርበታል፡፡

በመሆኑም ሚዲያዎቹ ለሀገራዊ ለውጡ አጋዥ ሚናቸውን ለመወጣት የሚያስችልና ነባራዊ ሁኔታውን መሰረት ያደረገ የአሰራር ፍልስፍና መከተል ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ በርካታዎቹ የሚስማሙበትና ለሀገራዊው ልማት መፋጠን እንደ ጠንካራ መሣሪያ የሚያገለግለው የልማት ጋዜጠኝነት የአሰራር ፍልስፍናን መከተል ይገባቸዋል ባይ ነኝ፡፡

እርግጥ ሚዲያዎቹ የልማት ጋዜጠኝነት የአሰራር ፍልስፍናን መከተል የሚገባቸው በዋነኛነት ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ነው፡፡ ይኸውም የአሰራር ፍልስፍናው ልማትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት አማራጭ የሌለው ብሎም ሀገራዊ ደህንነታችንን ለማረጋገጥ ፍቱን መድሃኒት  በመሆኑ ነው፡፡

የአሰራር ፍልስፍናውን መከተል ከፍተኛ የህዝብ ተሳተፎ እንዲኖር የማያስችል እንዲሁም የመንግስትን አሰራር ተጠያቂነትና ኃላፊነት የተሞላው እንዲሆን ከማድረግ አኳያ ሚናው የላቀ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገርም የልማት ጋዜጠኝነት ሙስናን በመዋጋት ልማትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲጎለብቱ የበኩሉን ሚና ይጫወታል፡፡

የልማት ጋዜጠኝነት ዋነኛ አጀንዳ ልማትን ማፋጠን ነው፤ ልማትን ለማፋጠን ደግሞ የህዝብን ተሳትፎ ማረጋገጥ ግድ ይላል፡፡ ከዚህ አኳያ የህዝብ ተሳትፎ ለማረጋገጥ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መኖር የማይታለፍ ጉዳይ ነው፡፡

እናም የሀገራችንን የፈጣን ልማትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ለማፋጠን የልማት ጋዜጠኝነት የአሰራር ፍልስፍናን መከተል አማራጭ የሌለው አማራጭ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ ውጪ ሚዲያው እንደ ሀገሩ ወፍ ላለመጮህ ከመፈለግ በመነጨ ከየትኛውም የፍልስፍና ዘውግ ጋር አብሮ የማይሄድ አሰራርን መከተል፤ ሀገራዊ ልማትንም ይሁን ስር እንዲሰድ የሚፈለገውን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ባህል ግንባታን ለማቀጨጭ ከመሞከር በስተቀር ሌላ ፋይዳ የሌለው መሆኑን መረዳት በጄ ነው። ምክንያቱም ከሀገራችን ፖለቲካል-ኢኮኖሚ ስርዓት ፍላጎት ውጪ የሚከናወን የሚዲያ አሰራር የማያወቁትን ሀገር የመናፈቅ ያህል ስለሚቆጠር ነው። ቸር ይግጠመን።